ክፍል 5

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

በባለፈው ጽሁፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ አጠቃላይ ይዘት እና የተወሰኑ ክፍሎችን በዝርዝር አይተናል። በዚህ ክፍል ቀሪዎቹን የመመሪያውን ይዘት እንደሚከተለው እንዳስሳለን፡

### የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ይዘት መስፈርቶች

የመመሪያው ምዕራፍ አራት የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ይዘት መስፈርቶችን በዝርዝር ያስቀምጣል ። እነዚህ መስፈርቶች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሽያጭ በሚቀርቡበት ጊዜ ይፋ መደረግ ያለባቸው ዓለም አቀፍ ምርጥ ልምዶችን እና ተሞክሮዎችን የሚያንጸባርቁ ናቸው።

መስፈርቶቹ የአውጪውን ደንበኛ ሳቢ መግለጫ የፊት ገጽ መግለጫዎችን፣ ማውጫ፣ ትርጓሜዎችን፣ የኮርፖሬት ማውጫን፣ የኃላፊነት መግለጫዎችን፣ የሶስተኛ ወገን መረጃ፣ የውጭ ኦዲተር ይፋ ማድረግን፣ የአውጪው መረጃ፣ አጠቃላይ የንግድ ሥራ መግለጫ፣ ገበያዎች፣ የቁጥጥር አካባቢ፣ሰራተኞች፣ የዕዳ ሁኔታ፣ ኢንቨስትመንቶች፣ ንብረት፣ ትልልቅ ኮንትራቶች፣ የፋይናንስ መግለጫዎች፣ የትርፍ ትንበያዎች፣ ጉልህ ለውጦች፣ ስለድርጅቱ አስተዳደር፣ የካፒታል መዋቅር፣ የትርፍ ክፍፍል፣ የተዛማጅ ወገን ግብይቶች፣ የቁጥጥር ድርሻ ያላቸው ሰዎች፣ የአስተዳደር አካላት ውይይት እና ትንተና፣ የአቅርቦቱ መጠን እና ዋጋ፣ ተገማች ስጋቶች እና የግብይት ዝግጅቶችን ያካትታሉ።

### የፊት ገጽ መግለጫ

የፊት ገጽ መግለጫው የአውጪውን ስም፣ የግብይት አማካሪ፣ የአቅርቦት አይነት፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ብዛት እና ዋጋ የሚገልጽ መሆን አለበት። እንዲሁም ባለሥልጣኑ የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን ማጽደቅ ትርፋማ ወይም አዋጭ መሆኑን ማረጋገጫ ተደርጎ ሊተረጎም እንደማይገባ እና ኢንቨስትመንቱ የስጋት መነሻዎች ስጋቶች ያሉበት መሆኑ በግልጽ መጠቀስ አለበት። በዚህ ረገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። የባለሥልጣኑ ሰነዱን ማጽደቅ የአዋጭነት ማረጋገጫ አለመሆኑ ወይም እንደ ኢንቨስትመንት ምክር እንዳይወሰድና በተሳሳተ መንገድ እንዳይተረጎም መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በመሆኑም ይህ መግለጫ በፊት ገጽ በግልጽ በሚታይ መልኩ በአቢይ (ካፒታል) ሆሄያትን በመጠቀም እና በደማቅ ፊደል በአግባቡ ጎልቶ በሚታይ መልኩ መጻፍ አለበት።

### የስጋት መንስኤ እና የቁጥጥር ሥርዓት

ሌላው የአውጪው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ አካል ለአደጋ መንስኤ ስጋቶችን ይፋ ማድረግ ነው። አደጋዎች ግልጽ እና ተዛማጅ መሆን አለባቸው፣ በግልጽ እና በአጭሩ የቀረቡ፣ የስጋት ቁጥጥር አሰራር የሚገልጹ፣ መሰረታዊ አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ የስጋት አይቶች ባላቸው ምድቦች በየአይነቱ የተደራጁ መሆን አለባቸው። የስጋት (ሪስክ) መግለጫ ለአደጋ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ መሰረታዊ ምክንያቶችን እና ሊያስከትሉ የሚችሏቸው አሉታዊ ተፅእኖዎችን መግለጽ አለበት። ይህም በሚሆንበት ጊዜ አቀራረቡን ላላ ባለ መልኩ ማድረግ ወይም "ይህ ላይሆን ይችላል" የሚሉ አገላለጾችን መጠቀም የተከለከለ ነው።

### የፋይናንስ አቋም መግለጫ

የአውጪው ደንበኛ ሳቢ መግለጫ የፋይናንስ አቋም መግለጫ ማካተት አለበት። ይህን በተመለከተ ትርፍ ወይም ኪሳራ እና ሌሎች አጠቃላይ ገቢዎችን፣ የባለቤትነት ድርሻ ለውጦችን፣ የገንዘብ ፍሰት መግለጫን፣ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎችን እና ማብራሪያዎችን ጨምሮ የተረጋገጡ ያለፉት አመታት የፋይናንስ መረጃዎችን የያዘ መሆን አለበት። የኦዲት ሪፖርቶች ገደቦችን፣ የሃሳብ ማሻሻያዎችን ወይም የኃላፊነት ማስተባበያዎች ወይም በጉዳዩ ላይ የተሰጡ አጽንኦት የያዙ ከሆነ፣ እነዚህ ሙሉ በሙሉ በምክንያት ተደግፈው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

### የስራ ካፒታል መግለጫ

ሌላው የአውጪው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ስለአውጪው የስራ ካፒታል በቂነት የሚገልጽ መሆን አለበት። አውጪው በቂ መሆኑን ማረጋገጥ በማይችልበት ጊዜ፣ ተጨማሪ የስራ ካፒታል እንዴት ለማግኘት እንደሚያስብ በጽሁፍ ማስረዳት አለበት። ይህ መስፈርት በቀጥታ የአውጪውን የቀጣይነት (ህልውና) አቅም የሚመለከት ሲሆን ኢንቨስተሮች አውጪው ካቀረበው ሰነድ ከሚገኝ ገቢ በላይ ተጨማሪ ካፒታል ሳይኖር መስራት ይችል እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። የመስፈርቱ ሁለትዮሽ ባህሪ ካፒታሉ በቂ ወይም እናሳ መሆኑን በደንበኛ ሳቢ መግለጫው በማብራራት ያለምንም አሻሚነት ግልጽ የሆነ መረጃ መስጠት ነው።

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ



## ዘላቂ ህልውና

ሌላኛው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ አካል የአውጪው የዘላቂ ህልውና ጉዳይ መግለጫ ነው። በዚህ ረገድ በደንበኛ ሳቢ መግለጫው የአውጪው የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የውጭ ኦዲተር ኩባንያው አገልግሎቱን ይዞ ወደ ፊት እንደሚቀጥል ወይም እንደማይቀጥል መግለጽ አለባቸው። ይህ መስፈርት በምስረታ ላይ የሚገኙ አውጪዎችን የማይመለከት ሲሆን የቦርድ አባላትን እና የኦዲተር መግለጫዎችን ኃላፊነት የሚያረጋግጥ ነው።

## ቀጣይነት ያለው ይፋ የማድረግ ግዴታዎች

ምዕራፍ አምስት፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸውን በይፋ ለሕዝብ ለሽያጭ ያቀረቡ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸው በሕዝብ የተያዙ አውጪዎች ቀጣይነት ያለው ይፋ የማድረግ ግዴታዎችን ይደነግጋል። የህግ ማዕቀፉ ወዲያው ይፋ የሚደረጉትን (ፈጣን ይፋ ማድረግ የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ክስተቶች) እና ወቅታዊ ይፋ ማድረግ የሚያስፈልጋቸውን (ሩብ ዓመታዊ እና ዓመታዊ የፋይናንስ መግለጫዎች) ያካትታል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች እና ሕዝቡ የአውጪውን አቋም ለመገምገም፣ሐሰተኛ ግብይቶችን እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ለማስወገድ እንዲያስችል አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ይፋ መደረግ አለበት። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ክስተቱ በተፈጠረ ወይም ከታወቀ በኋላ በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት መደረግ አለበት። የመመሪያው አንቀጽ 139 ይፋ መደረግ የሚገባቸውን መረጃዎች በስድስት ምድቦች ከፍሎ ያስቀምጣል።

ከእነዚህ መካከል የአስተዳደር እና ሥራ አመራር ጋር የተገናኙ ጉዳዮች፣ የአውጪው እና ተቀጽላዎቹ ንብረቶች እና እዳዎች ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ሰዎች፣ የንግድ ስራዎች እና አፈፃፀም፣የብድር ዝግጅቶች፣ ከውጪ ኦዲተር እና ከፋይናንስ መግለጫ ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች እና የካፒታል መዋቅር ጉዳዮች ይገኙበታል። ለመዘርዘር ያህል በእያንዳንዱ መደቦች ውስጥ የኩባንያው ቦርድ እና ሥራ አመራር አባላት ለውጥ፣ የኩባንያው ቁጥጥር የሚያበቃ ድርሻ ያላቸው ሰዎች ለውጥ እና መረጃዎቻቸው፣ በመመስረቻ ጽሑፉ የተደረጉ ለውጦች፣ የውህደት እና ግዥ ማሳወቂያ መቀበል ወይም መስጠት፣ የእዳ ግዴታ ውስጥ መግባት፣ ዋና ባለድርሻ መክሰር፣ ትልቅ የገንዘብ መጠን የያዙ ውሎች መፈራረም ወይም መቋረጥ፣ ንግድ ሥራ ላይ ተጽዕኖ ያላቸው አዳዲስ ህጎች መውጣት፣የደንበኛ መክሰር፣ ከአበዳሪዎች ጋር እዳ መልሶ ለማዋቀር የሚደረጉ ስምምነቶች ውድቅ መደረግ እና የአበዳሪዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ የእዳ አቋም ላይ የተደረጉ ለውጦች፣ የውጪ ኦዲተር ለውጥ እና ምክንያቶቻቸው፣ በአውጪው የተደረጉ ያልተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭ፣ እነዚህ እና የመሳሰሉት ወዲያው በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ይፋ መደረግ ያለባቸው መረጃዎች እንደሆኑ በመመሪያው ተመልክቶ ይገኛል። በተጨማሪ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ እንደሚያሳየው "ፈጣን" ይፋ ማድረግ የሚበረታታ ልምድ መሆኑን ነው።

ሌላው የአውጪው ወቅታዊ መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ግዴታ ሲሆን በየሩብ አመት የፋይናንስ መግለጫዎችን ይፋ ማድረግ ይጠበቅበታል። በተጨማሪ አውጪው በሂሳብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በ90 ቀናት ውስጥ ዓመታዊ ኦዲት የተደረጉ የተረጋገጡ የፋይናንስ መግለጫዎችን ይፋ ማድረግ አለበት። በዚህ ሂደት አውጪው በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የማኔጅመንቱ ውይይት እና ግንዛቤ፣ ዓመታዊ የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ-ጉባኤዎችን፣ የቦርድ ሊቀመንበሩን መግለጫ፣ የቦርድ ኃላፊነት መግለጫ፣ የውስጥ ቁጥጥር እና የኮርፖሬት አስተዳደር ሪፖርቶችን እና ሌሎች መረጃዎችን የያዘ ዓመታዊ ሪፖርት ይፋ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ከላይ የተጠቀሱት የሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ሰሌዳዎች (የሃያ አራት ሰዓት እና ዘጠና ቀናት) የተለጠጡ ቢመስሉም አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ባገናዘበ መልኩ የተደራጁ ናቸው ማለት ይቻላል።

ሌላው የአውጪውን የገቢ ትንበያ የተመለከተ ሲሆን ማንኛውም አውጪ የሂሳብ ዘመኑ ከመጀመሩ ከሃያ ቀናት በፊት የገቢ ትንበያውን ለባለሥልጣኑ ወይም ሰነዶቹ ለተመዘገቡበት እና ለሚገበያዩበት ገበያ ማሳወቅ ይችላል። ትንበያዎቹ ከሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ጋር መጣጣም፣ መሰረታዊ ግምቶችን መግለጽ እና በዋና ሥራ አስፈፃሚ እና በዋና የፋይናንስ ኦፊሰር የተረጋገጡ መሆን አለባቸው። አውጪው ቀደም ሲል የወጣ ትንበያ ከነበረው እና ያንን ትንበያ ማሟላት ካልቻለ፣ ወዲያውኑ ይህንኑ ከምክንያቶቹ ጋር ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት።

የገቢ ትንበያ ይፋ ማድረግ አውጪዎች በፈቃደኝነት መረጃ ማቅረብ እንዲችሉ እድል የሚሰጥ ነው። ይሁን ኢንጂ አውጪዎቹ የገቢ ትንበያውን ይፋ ካደረጉ በኋላ ትንበያው ሊደረሱበት በማይችሉበት ከሆነ ወዲያውኑ ተጠያቂነትን ይፈጥራል።

## ከምዝገባ ነፃ ስለመደረግ

### በግል ለሽያጭ ማቅረብ

በካፒታል ገበያ አዋጅ መሰረት ለግል ሽያጭ ማቅረብ ማለት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሳያቀርቡ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ኢንቨስተሮች ብቻ ማቅረብ መሆኑ ተደንግጓል። ይህን የአዋጁን ድንጋጌ ተከትሎ በወጣው መመሪያ መሰረት ለግል ሽያጭ ማቅረብ የሚከናወነው ከሃምሳ ላልበለጡ አስቀድሞ ለተወሰኑ ኢንቨስተሮች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በመሸጥ እና የሚሰበሰበውም አጠቃላይ ገንዘብ ከአንድ መቶ ሚሊዮን ብር የማይበልጥ ሲሆን ነው። በግል ለሽያጭ በቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭ ሂደት ማስታወቂያ ማስነገርም ሆነ ማውጣት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በግል ለሽያጭ የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በኋላ ላይ ካልተመዘገቡ በስተቀር ለሕዝብ በይፋ ሊሸጡ አይችሉም። የሃምሳ ኢንቨስተሮች እና የመቶ ሚሊዮን ብር መስፈርቶች ግልጽ የሆኑ ገደቦችን የሚጥሉ ናቸው። በዚህ ሊነሳ የሚችለው ሌላው ጉዳይ እነዚህ በግል ለሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከምዝገባ መስፈርቶች ነጻ መደረጋቸው ነው። በመሆኑም በዚህ ሂደት አውጪው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማዘጋጀትም ሆነ በባለሥልጣኑ ማጸደቅ፣ የግብይት አማካሪ ተቋም መሾም አይጠበቅበትም። በተጨማሪ ለህዝብ ሰነደ ሙዓለ ንዋያቸውን ለሚያወጡ እና ለሽያጭ ለሚያቀርቡ አውጪዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቅባቸው ሌሎችም የምዝገባ መስፈርቶች ሰነደ ሙዓለ ንዋያቸውን በግል ሽያጭ በሚያቀርቡት ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

### ብቁ ኢንቨስተሮች

በመመሪያው መሰረት ብቁ ኢንቨስተሮች የሚባሉት ተቋማዊ ኢንቨስተሮችን እና አንድ ቤት መኪና እና አንድ መኖሪያ ቤት ሳይጨምር የተጣራ ሀብታቸው ቢያንስ አስር ሚሊዮን ብር እና ከዛ በላይ ያላቸውን ሰዎች ናቸው። ተቋማዊ ኢንቨስተሮች የምንላቸው ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች፣ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት፣ የፌደራል እና ክልል መንግስታት፣ የጋሪዮሽ የኢንቨስትመንት ፈንዶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የጡረታ ፈንዶች እና ሌሎች ባለሥልጣኑ ተቋማዊ ኢንቨስተር ናቸው ብሎ የሚመድባቸውን ኢንቨስተሮች ያካትታል።

አውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን ለሽያጭ የሚያቀርበው ለእነዚህ ብቁ ኢንቨስተሮች ሲሆን የብቁ ኢንቨስተሮቹ ቁጥር በባለስልጣኑ ካልተፈቀደ በስተቀር ከአንድ መቶ መብለጥ የለበትም።

በዚህ ሁኔታ ሰነደ ሙዓለ ንዋያቸውን ለብቁ ኢንቨስተሮች የሽያጭ ያቀረቡ አውጪዎች የኢንቨስተሮቹን ሁኔታ፣ የኢንቨስተሮቹን ብቃት ማረጋገጥ፣ ከኢንቨስተሮቹ የተፈረመ ማረጋገጫ ማግኘት፣ እና መረጃዎቹን ለአስር ዓመታት መያዝ አለባቸው። በዚሁ አካኋን የተሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሌሎች ብቁ ኢንቨስተሮች ካልሆነ በስተቀር ወይም ካልተመዘገቡ በስተቀር ሊተላለፉ አይችሉም።

ይህ የብቁ ኢንቨስሮች የህግ ማዕቀፍ ልምድ ያላቸው ኢንቨስተሮች ከመደበኛ (Retail) ኢንቨስተር ያነሰ ቁጥጥር እና ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያመላክት ነው። በመሰረቱ የአውጪውን ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማዘጋጀት፣ ማስጸደቅ እና በባለሥልጣኑ ምዝገባ ማድረግ መደበኛ ኢንቨስተሩ ከአውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በሚገዛበት ጊዜ ስለ አውጪው በቂ መረጃ ኖሮት እና አውቆ እንዲገዛ ለማድረግ የሚረዳ የጥበቃ ዘዴ ነው። በዚህ ረገድ ብቁ ኢንቨስተር ሲሆን የአውጪውን ደንበኛ ሳቢ መግለጫ ማየት ሳያስፈልገው ባለው ልምድ እና ክህሎት ብቻ በመጠቀም የአውጪውን ሰነዶች አዋጪነት ሊያውቅ የሚችል በመሆኑ አውጪው ደንበኛ ሳቢ መግለጫ በባለሥልጣኑ እንዲያስጸድቅ እና ብቁ እንቨስተሮች እንዲያዩት ማድረግ እምብዛም አስፈላጊ ካለመሆኑ ባሻገር ከምዝገባ አስፈላጊነት አላማ አንጻር የሚጠበቀውን ጥበቃ የሚሰጥ አይሆንም። ከዚህ በመነሳት በብቁ ኢንቨስተሮች መካከል የሚደረግ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ኢንቨስተሮቹ በልምድ እና ብቃት የተሻሉ በመሆናቸው የሚያስፈልጋቸው ጥበቃ በአንጻሩ ከመደበኛ ኢንቨስተሩ ያነሰ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

### አነስተኛ አቅርቦቶች

ሌላው አውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን በመሸጥ የሚሰበስበው እስከ አስር ሚሊዮን ብር ብቻ ከሆነ አነስተኛ አቅርቦት በመሆኑ ከምዝገባ ነጻ ይደረጋል። በእንደዚህ አይነት አቅርቦቶች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሽያጭ ማስታወቂያ ከማስነገር እና ማውጣት የተከለከሉ ናቸው። እነዚህ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ብቁ ለሆኑ ኢንቨስተሮች ወይም ከምዝገባ በኋላ ካልሆነ በስተቀር ሊተላለፉ አይችሉም። እስከ አስር ሚሊዮን ብር አነስተኛ አቅርቦት ከምዝገባ ነፃ መደረግ በጣም አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያለ ምዝገባ ካፒታል እንዲሰበስቡ እድል የሚሰጥ ነው።

በቀጣይ ጽሁፎች ቀሪ የሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ክፍሎች ዳሰሳ በስፋት እና በጥልቀት የምንቀጥልበት ይሆናል።